# ችግር የቤት ልጅ ሆነብንሳ?

ሙሊሳ ጫላ (ሰሜን አሜሪካ)

ችግር በማያባራ መንገድ የጠበሰው የሀገራችን ሰው በምጸት ችግር የቤት ልጅ ነው የሚል አባባል አለው ። ደባል ሆኖናል ማለትም ኔው ። የ አሲምባ ድረ ገጽ አዘጋጆች ስለ ችግራችን ጻፉ እንወያይ ብለው ጥሪ አቅርበዋልና ለውይይቱ ይረዳ ዘንድ በበኩሌ አንዳንድ  ችግር ሆኑ የምላቸውን ትዝብቶች ላቀርብ እፈልጋለሁ። ለመጠንከር ሀቁን መቀበል መናገር ተብሏልና ይህን ጎዳና ስንከተል የሚቀየሙና የሚቆጡ ካሉ አደብ ግዙ ማለቱ ከወዲሁ አስፈላጊ ነው ። ጣኦት አንጥረብ እንደተባለው ሰዎችን የማይተቹና የማይወቀሱ አድርገን--አይገሰስ አይከሰስ ዓይነት-- ከተቀበልን እርምት ማድረጉ ይከብዳል፤ ድከመት ችግር እውነትም የቤት ልጅ ሆኖ ይከርምብናል ።

ችግራችን ምንድነው?

- ከራሳችን ታሪክ መማር አለመቻል ። አጼውን ብልህ ታላቅ ብሎ ምስላቸውን በደረቱ ለጥፎ የሚወዘወዝ ወጣት ጥቂት አይደለም። የአጼው ስርዓት ግን ሕዝብን የበደለና ያሰቃየ ከፉና ኋላ ቀር መሆኑን ዘንግተዋል ። እነ አርበኛ በላይ ዘለቀን፤እነ መንግስቱና ና ገርማሜ ንዋይን፤ወርቅነህ ገበየሁን፤ ተማሪዎች ጥላሁን ግዛውንና እነ ዋለልኝን ሁሉ የገደለው የአጼው አገዛዝ መሆኑን መርሳት ኤንዴት ይቻላል ? ፋሺስቱ ና ጨፍጫፊውን መንግስቱን ጀግና ለማለት መቃጣትና በሰማዕት ደም መቀለድ ። የወያኔንም ማንነትና ግፍ ሁሉ መርሳትና ቸል ማለት --እንዴትስ ይፈቀዳል ?
- ይህ ወዴት ያመራል? ጠላትና ወዳጅን መለየት ማቃትን ያስከትላል ። ውዥንብርን ያሰፍናል ። ትላንትን የረሳ ስህተቱን ይደግማል ነውናም ስህተትን መድገምና መንዳት ይከተላል ። ከ1966 አብዮትና ከተከተለው የተገኘውን ትምህርት መርሳት ለ1997 ምት አጋልጦናል ። ከ1997ኡ አለመማር ደግሞ እስከዛሬም ጠምዶና ቀይዶ ሲያሽመደምደን እየታየ ነው ። ትግል እንዴት? መሪ ማነው፤ እነማን ናቸው? ጠላቶቻችንስ እነማን ይባላሉ?  ወዘተ. …. ሁሉን በተመለከተ የጠራ ግንዛቤ መያዝ ከቶም አልተቻለም ። እነ ክህደቱ ብቻ ሳይሆኑ እንደ በየነ ጴጥሮስ ዓይነቶቹ አድርባዮችም ግራ አጋብተው ለወያኔ ሰለባ አደረጉን ። ከበየነ ጋር ቆሞና ለአሜሪከና

እንግሊዝ ተገዢ ሆኖ የሙት ከተማ አድማውን ያከሸፈው ዛሬም የትግል መሪ ነኝ ብሎ ሲሞካሽ አጨብጫቢዎች አልጠፉም ። ከወያኔ ጋር ሆነው ጦርነት እንሰራባችኋለን ሲሉና ነፍስ ሲያጠፉ የቆዩትንም ያመረሩ ወያኔዎች ጀግና አርበኛ ብለው ሊያስተናግዱ ደፋ ቀና ያሉና ያዋረዱን ጥቂቶች አልነበሩም ። በአጭሩ መሪዎቻችን ሊሆኑ የሚችሉትን ሰዎችም ለይተን ማወቅ አልቻልንም። በመሆኑም የፖለቲካውን መድረክ የኢሰፓ ነፍሰ ገዳዮችና ታጣቂ ካድሬዎች፣ የመንግስቱና መላኩ ተፈራ አጫዋቾች፣ የወያኔ ሰርጎ ገቦች፣ ድርጅት አፍራሽ አንጃዎችና ዘመናዊ ባንዶች፣ የነ አቦይና አለቃ አገሌ ልጆችና ደሞዝተኞች እየፈነጩበት ናቸው ። ጥቃታቸውም ለወያኔ ጠላት ሆነው ባስቸገሩት ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ያተኩራል ። ዛሬ ጸረ ኢትዮጵያ ሆኖ የቆየው ጃዋር ወጥና ደም እስኪረግጥ ድረስ ሲያደንቁት የከረሙት ብዙዎች መሆናቸውን የምንረሳው አይደለም ። ዛሬ ለምሳሌ በኢሕአፓ የተወሰኑ መሪዎች ላይ ከየአቅጣጫው ጸያፍ የስም ማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደና ድርጅቱን ለማፍረስ አዳዲስ ሴራዎች እየተሸረቡና የቴሌፎን ስብሰባዎች እየተካሄዱ ናቸው ። መሰረቱ ከድርጅቱ የተወሰኑ ግለሰብ መሪዎችን ላይ ዘምተን ከመታናቸው ድርጅቱ ይፈርሳል የሚል ቅዠት ነው ። ይህም የአመራርን ወሳኝ ጥያቄ ወደፊት ያመጣዋል ።

- ትግልን ወደ ድል ለመውሰድ መደራጀት ወሳኝና ቀዳሚ ነው ። ድርጅትን ደግሞ ለማታገል ጽኑ አባላትና ጠንካራ አመራር ያስፈልገዋል ። አመራር ብቻውን ብዙ አይፈይድም፣ አባላትም በሙሉ አቅማቸውና ችሎታቸው ይታገሉ ዘንድ ብቁ አመራር ያስፈልጋቸዋል ። የወያኔ ቅጥረኞች ድርጅቶችንና አመራራቸውን የሚያጠቁት ድርጅቶቹን ለማኮላሸት ነው ። መተቸት በሚገባቸውና የወያኔም የምዕራቡም ቅጥረኛ የሆኑትን ትተው፣ የሻዕቢያ ስናር አህያ  የሆኑትን ወደጎን አድርገው ፣ ትኩረታቸው ወያኔን እየታገሉ ባሉት ድርጅቶችና መሪዎች ላይ ሆኖ ሲገኝ ግለሰቦቹ ወደዱም ጠሉም የሕዝብን ትግል ተጻራሪዎችና አፋኞች መሆናቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል ። ወደዱም ጠሉም

  በእውነቱ ! ሕዝብ ብቁ አመራሮችን ሊሰይም ካልቻለና በ አስመሳዮች፣ አድርባዮችና አልፎም ከሃዲዎች ተታሎና መሪዎች ብሏቸው አቅፎ ሊመራ ከተነሳ ጥፋቱ የራሱ ነው ። ሁላችንም እንደምንታዘበው ዋና ፖለቲከኞች ነን ብለው በአሁኑ ጊዜ የሚቧርቁብንና  ዜንችም ሀይ ሀይ የሚሏቸው ግለሰቦች ብቃት የሌላቸው ግለሰቦች ናቸው ። መዝፈን ሌላ ፖለቲካ ሌላ"" መሮጥ ማሸነፍ ሌላ ፖለቲካ ሌላ። ይህ አልባል ብሎ እኮ ነው ለምሳሌ--መለስ ባይወደውም-- የወያኔ መጋዣ የሆነው ሀይሌ ገብሬ ስላሴ ፕሬዚዳንት ልሁንባችሁ የሚለን! ይህንንም መሸከም

አለብን? ለምን? እስከመቼስ? የፖለቲካው መድረክ ሲደፈርስ ወያኔ ጮቤ ይረግጣል ። ሰርጉ ነው ። ውዥንብር መስፈኑ ይጠቅመዋል ። በዚህ በዚያ ድርጅቶችንና መሪዎቻቸውን እያጠቁ ያሉት ውድቆች ደግሞ ወያኔ የቀጠራቸውና አሊያም ወዶ ገብ አገልጋዮቹ ናቸው ። ለወያኔ ወፍጮ ባቄላ አቅራቢዎች ። ይህ ማን የእኛ ነው? ማን መሪ ነው? ማን የህዝብ ደርጅት ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት አለመቻል የሕዝብን ትግል በኣያሌው ጎድቷል ። እነጃዋር መሀመድ ዓይነቶች ዘረኞች፡ እነ ስየ አብርሃ ዓይነት ወንጀለኞች ፤ የደርግ ነፍሰ ገዳይ ካድሬዎች፤ ድርጅት አጥቂ አንጃዎች፤ ማፈሪያዎችና የባዕድ ሰላዮች ሁሉ መሪ፤ ሕዝባዊ፤ ጀግና ታጋይ የተባሉበት አስፋሪ ሁኔታ ተከስቷል ። ይህ አንዱ ሌላ ዋናው ችግራችን ነው ።

- እንቀጥል ። ሌላው ችግራችን ጠባብ ብሄረተኞችና ጽንፈኞችን የመሸከም ዝንባሌያችን ነው ። ያወቅነውን ሀቅ አላወቅንም ማለት ። ለዚህም ነው ለዘመናት ገንጣይና የጥላቻ ቋት ሆነው የቆዩትን ኦነግ መስል ቡድኖች ለማቀፍ ጥረቶች ሲደረጉ የቆዩት። ባዕድ ነን ፤ አላማችን መገንጠል ነው የሚሉትንም ጭምብል አልብሰውና ኢትዮጵያዊ ናቸው ብለው ገብያ ሲያወጧቸው ታዝበናል ። ዛሬ በየማይረባው መድረክ የሚገኙ ምሁር በሉን ባዮች ቀፎዎች መላ የኦሮሞ ሕዝብ ኦነግ ነው ብለው ሊያሳምኑንም ሞክረው ነበር ። ኦነግ--ሁሉም አንጃ--ከጠባብና ባዕድ ነን አቅዋሙ ከቶም ፈቅ አላለም ። ጃዋር የዚህ ጠባብነት ጺያፍ ክስተት ነው ። አሜሪካም ሻዕቢያም አልተለወጡም ። ጸረ ኢትዮጳያ ናቸው ። እነዚህን ረዳትና ታዳጊ ብሎ መገመትና መጠበቅ ደግሞ ሀገርን ጎጂ ጅልነት ነው ። ሻዕቢያን አምነው በአርበኞች ግንባር ዙሪያ የተሰበሰቡት ዜጎች ወይ እንደነ ተስፋዬ ጌታቸውና ሌሎቹ ተገድለዋል አሊያም ታስረው ደብዛቸው ጠፍቷል ወይም በሚጠቅም መንገድ እንዳይንቀሳቀሱ ታግደዋል ። በ ኤርትራ "ሕዝባዊ ሐይሎችን " መሰረትን ያሉን ገንዘብ ነጣቂዎች ደግሞ እዚህ ከዚያ ቃርመን የአስር ሰው ጋንታ ልናሰማራ ነው ብለው ያሾፉብናል እንጂ ጦር ያሉት ልብወለድ ሆኖ ቀርቷል--ማታለያ ማደናገሪያ ። የለየለትና ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚለው ዳውድ ኢብሳና የኦጋዴን መሰሎቹ በአንጻራዊ ደረጃ ይሻላሉ-- ኢትዮጵያን ማፍረስ መገንጠል ነው አላማችን ሲሉ በግልጽ ቆመዋልና። ከነ ከማል ገልቹ፤ ሌንጮ ለታ ተራ ሽወዳ የተሻለ ነው ። ቢከፍቱት ተልባ መሆኑን የሲአይኤ ቅጥረኛው ጃዋር እነሆ = ለአላህ ምስጋና ይግባውና -- የጥላቻ ዛሩ እያስጎራው ማንነቱን (ማንነታቸውን) ግልጽ አድርጎ አቅርቦልናል ። የበደኖና አሰቦት፤ የአሶሳ ወንጀለኞችን ነጻ ኣውጪ ብሎ ማሞካሸትና ጸረ ኢትዮጵያ ኣቅዋማቸውን ለመደባበቅ መነሳት ጸረ ኢትዮጵያነትን ማጀብ ነው ።

- ችግራችን በመሰረቱ ወያኔ መሆኑ ክርክርን አይጠይቅም ። ይህ ግን ግልጽና የታወቀ ነው ። ወያኔ ይጠራናል ኑ ግቡ ይለናል ብለው በአፍጢማቸው የተደፉ ያን የምትሐት ጥሪ እስካሁንም እየጠበቁ ናቸው። ወያኔ ግን ንቋቸው ቢዘጋቸውም እነሱ የወያኔ ጠላት ድርጅቶችና መሪዎችን እያጠቁ አቦይ ጌታችን እየን እንጂ ላንተ ስንል ስንዳከር እያሉት ናቸው ። ከንቱ ልፋት ። የወያኔን ህግ ህገ መንግስት ብለው ይከበርልን የሚሉ ክፍሎች ስለ ፖለቲካው ሁኔታ ምንም ማወቅ የተሳናቸው ናቸው ። ወያኔን የኢትዮጵያ መንስትም ብለው የሚጠሩ ወይም ወያኔን በሚመቸው ጭንብሉ ኢሕ አዴግ የሚሉት ሁሉ ለወያኔ አውቁም አላወቁም እጅ የሰጡ ናቸው ። በፖለቲካ መስክ ቃል ትርጉምና ክብደት አለው። መሌ፤ ወዩ፤ መንጌ የጸረ ሕዝቦች ቋንቋ ነው ። ከወያኔ ጋርም በዛሬው ጊዘ እርቅን የሚሰብኩ ደግሞ ሕዝብን ከወሳኝ ትግሉ ሊያፈናቅሉ የሚሹና--ወደዱም ጠሉም-- ለወያኔ እየጠቀሙ ያሉ ናቸው ። በየ ድረ ገጹ ስንት ውሸት አነበብን ? ጎንደርስ ስንቴ ነጻ ወጣ? ኢምንት ቡድኖች ስንት ሺውን በወረቀት አሰለፉ? ብጸረ ወያነ ድርጅት መሪዎች ላይ ስንቱ ጸያፍ ክስና ውሸት ተደረደረ? ችግራችን ሀቅን ማወቅና ማስፈን አለመቻላችንም ነው ።

ይቀጥላል......................

ሙሊሳ ጫላ (ሰሜን አሜሪካ)